
# ናይል



Nile 8th year; publication No.1 January,2022

ናይል 8ኛ ዓመት፣ ቁጥር 1፣ ጥር 2014 ዓ.ም




## ወቅቱን የዋጀ አነቃቂ መድረክ

በሙሉጎጃም አንዱዓለም

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከውጭ ጉዳይ ሚንስቴር ጋር በመተባበር “ሐሰተኛ መረጃ በኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ያሳደረው ጫና እና መፍትሔው” በሚል ርዕሰ-ጉዳይ ላይ ያዘጋጀው የምክክር መድረክ በዩኒቨርሲቲው ጥበብ ህንፃ የመሰብሰቢያ አዳራሽ የውጭ ጉዳይ ቃል አቀባይ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ ጨምሮ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት፣የዩኒቨርሲው ከፍተኛ አመራሮች፣ የተለያዩ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዘዳንቶች እና ተጋባዥ እንግዶች በተገኙበት ባሳለፍነው ታህሳስ ወር በድምቀት መካሄዱ ይታወሳል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዘዳንት ዶ/ር ፍሬው ተገኘ በመክፈቻ ንግግራቸው አሸባሪው የትግራይ ወራሪ ኃይል በምዕራባውያን ሀገራት በመታገዝ የሚያሰራጨት የሐሰተኛ መረጃ ማዕበል፡-

“አባቱ ዳኛ ልጁ ቀማኛ

ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮሓል

ወደ ገፅ 3 ዞሯል




## በውስጥ ገፆች

“የትምህርት ጥራት መውደቅ እና ለውድቀቱ ባለቤት ማጣት” 4
የገዞ ማስታወሻ 11
ህዝቡ በባዶ እጁ ከስናይፐር ጋር ተናንቆ... 7
“ያለምሁራን ተሳትፎ...” 15
University-Industry Linkage 14
በህልውና ዘመቻው የተማሪዎች ተሳትፎ 9




# ናይል

በኢንፎርሜሽን ስትራቴጂክ ኮሚዩኒኬሽን ም/ፕሬዘዳንት ጽ/ቤት
የውስጥ ግንኙነት እና ኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የሚዘጋጅ ወርሀዊ ጋዜጣ

**ዋና አዘጋጅ**

ትዕግስት መኮንን

**ግራፊክስ ዲዛይነር**

ትዕግስት መኮንን

**ዘጋቢዎች**

ሙሉጎጃም አንዱዓለም
ወንዳለ ድረስ
ሙሉጌታ ዘለቀ
ባንቹ ታረቀኝ
ሸጋው መስፍን

**ፎቶግራፈሮች**

አገሬ ዘለቀ

ታምራት አታላይ
በሪሁን ታረቀኝ
ቤተልሄም ወርቅነህ

**አምደኞች**

ደስታ ተከስተ
አስራት ደርብ

**አርታኢ**

ግርማው አሸብር
አለባቸው አለሙ

**ስርጭት**

የመረጃ ዴስክ ባለሙያዎች
**አለነ ጋሹ**

**ፀሀፊ**

መልሰው አደመ
አበባ ካሳው

**ሾፌር**

ላመስግን ጫኔ
**አራጋው በሪሁን(ቸሬ)**

Contact us:-

https://www.bdu.edu.et
http://www.twitter.com/bdueduet
https://www.facebook.com/bduethiopia
http://www.linkedin.com/school/bahir-dar-university
+251583209653

**አባይ ማተሚያ ቤት**
**ታተመ**
**ጥር 2014 ዓ.ም**

# ርዕሰ-አንቀጽ

## የትምህርት ዘርፉ ከፖለቲካ አቢዮት ጸመኛ መሆን አለበት

የኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርት ከተጀመረበት 19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ገደማ ጀምሮ እስካሁን ድረስ የኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርት ሀገረኛ ጣዕምና ቅርጽ ሳይኖረው አንድ ምዕተ ዓመትን አስቆጥሯል::አንድ ክፍለ ዘመን ሲጓዝ የአገሪቱን ዜጎች በሙሉ ከዱካ ፊርማ አላዳነም፣ ከባዶ እግር መራቆት ነጻ አላወጣም፣ ኋላቀር አስተሳሰብን አሸንፎ የስልጣኔ ችቦን በመለኮስ የመሃይምነት ጨለማን አልገረሰሰም::

ለዚህም በተለያዩ ጊዚያት ውስጥ በአገሪቱ የተካሄዱ የፖለቲካ ስርዓት ለውጦች በትምህርት ተቋሙ ላይ የራሳቸውን ብትር አሳርፈዋል:: በማህበረሰብ የኑሮ ዘዴ ለውጥና የአገር ግንባታ ላይ ትምህርት ስርዓቱ የአንበሳውን ድርሻ እንዲወጣ የመጀመሪያውን የአፍራሽነት ሚና የፖለቲካ ለውጦች አብዮታዊነት ይወስደዋል::

ራቅ ያለውን ትተን አሁን ያለንበትን ዘመን ለአስረጅነት ለማሳየት ያህል የኢህአዴግ ስርዓት የደርግን ስርዓት በሀይል ንዶ ሲገባ የትምህርት ስርዓቱንም ከመናድ አላረፈም:: እንዲያውም የመማሪያ መጻህፍት ጭምር ተቃጥለዋል:: የስርዓተ ትምህርት ለውጥም የፓርቲ ማኒፌስቶ ለማስፈጸምና ለማስረጽ በሚረዳ መልኩ ተቀርጸዋል:: በዚህ ዘመንም የስርዓት ለውጥ ኢህአዴግ ብልጽግና ሲሆን የኢህአዴግ ፈጣሪዋ ህወሐት በተከፋች ጊዜ የትምህርት ተቋማትን ማቃጠልና መዝረፍ፣ ምሽግና የጦር ሜዳ በማድረግ ሁለቱ ሀይሎች ሲፋለሙበት ተመልክተናል::

ተማሪዎች በምግባራቸው ተሻሽለው ፣ ለሀገር ግንባታ ብቁና ብስል ዜጋ ከመሆን ይልቅ በትምህርት ተቋማት ውስጥ ተዘርግቶ በነበረው የፖለቲካ ፓርቲዎች አደረጃጀት የካድሬነት ተግባርን ሲለማመዱና ሲፈጽሙ የነበሩትን ብንመለከት ቀላል የሚባሉ አይደለም:: በትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚፈጠሩ የተማሪዎች የእርስ በርስ ግጭቶችም የፖለቲካ ፓርቲዎች እጅ ረዝሞ ዩኒቨርሲቲዎች ደጅ በመድረሱ ነው::

ከቅርብ ጊዜ ትዝታዎቻችንና አሁን ካለንበት ሁኔታ ላይ አስረጅ ለመጥቀስ ይሞከር እንጂ ሀገራዊ፣ ቀጠናዊና አለም አቀፋዊ ጫናዎች ሁሉ ገና ከመሰረቱ በኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርት ላይ የራሳቸውን የጭቆና በትር አሳርፈዋል:: በመሆኑም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የተጣለባቸው የፖለቲካ መንፈስ መስበርና የራሳቸውን ሀገራዊና ቀጠናዊ ሚና እንዲወጡ ማስቻል ከዜጎች ጀምሮ እስከሀገረ መንግስቱ ውሳኔ ሰጪ አካላት መረባረብ ይጠበቅባቸዋል::

ትምህርት የሀገረ መንግስት መሰረት መጣያ መሳሪያ እንጂ በየዘመናቱ ለሚፈጠሩ የፖለቲካ አደረጃጀቶች መሸፈቻ ጫካ መሆኑ መብቃት አለበት:: ተማሪዎች፣ መምህራንና ተመራማሪዎች በጥቅሉ የትምህርት ማህበረሰቡ ከዚህ ዳፍንት ነጻ ለመውጣት መጀመሪያ ራስን ነጻ አውጥቶ የመረረ ትግል ማካሄድ ይጠበቅበታል::

ያ ሲሆን ሀገር ሲከፋት አይዞሽ የሚላት፣ ትውልድ ሲጎድል የሚተካ ፣ አቅም ሲንገዳገድ የሚደግፍ የተማረና የበሰለ አዲስ ዜጋ ከትምህርት ተቋሞቻችን ማምረት እንጀምራለን::

በመሆኑም የትምህርት ተቋማት ከፖለቲካ ፍጹም ጸመኛ መሆን አለባቸው::

## ወቅቱን የዋጀ … ከገፅ 1 የቀጠለ

ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው”እንዲሉ የሐሰተኛ መረጃ ከእውነተኛው በበለጠ መልኩ ስለሚሰራጭ ምሁራኑ በእውቀትና በጥበብ እውነታውን ለማሳወቅ ጉልህ ድርሻ እንዳላቸው አሳስበዋል:: የእለቱ የክብር እንግዳና የጠቅላይ ሚንስትሩ የማህበራዊ ጉዳይ አማካሪ ሙዓዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት በኢትዮጵያ ላይ የሚስተዋለው የሀሰተኛ መረጃ ምንጩ ስህተት ሳይሆን ሆን ተብሎ የተደረሰ በምራባውያን ሀገራት ፍላጎት የሚዘወር ድርሰት መሆኑን ሲያብራሩ የሀሰተኛ መረጃ ዘመቻው በስለላ ድርጅቶች፣ በእርዳታ ድርጅቶች፣ በብዙሀን መገናኛ ተቋማት እና በፖለቲከኞች የሚተወን ቲያትር ሲሆን ዓላማውም እርስ በእርሳችን ማባላት፣ማጋጨት እና ሀገር አልባ ማድረግ ነው ብለዋል:: ዘመቻውን ለመቀልበስ እነዚህ የውጭ አካላት ኢትዮጵያ ላይ ያላቸውን እይታ እንዲቀይሩ ከመጠበቅ ይልቅ እኛ ኢትዮጵያዊያን ስለእነርሱ ያለንን እይታ ለመቀየር “ዓለም አቀፉን ማኅበረሰብ የምንመለከትበት መነጸር ሊቀየር ይገባል” በማለት ዲያቆን ዳንኤል ምክረ ሀሳባቸውን ሰንዝረዋል:: በተጨማሪም እንደ “BBC“እና “CNN” የመሳሰሉት ሚዲያዎች የግል የንግድ ድርጅት እንጂ የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ሚዳያዎች ስላልሆኑ “ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን” የሚል የክብር ስም መሥጠት የለብንም ብለዋል:: እኛ ኢትዮጵያዊያን ይላሉ ዲያቆን ዳንኤል የውጭ ኀይሎችን የቲያትር ድርሰት ተመልካቾች መሆናችንን ትተን የራሳችንን እውነታ ፀሐፊዎች የምንሆንበት ታሪካዊ ወቅት ላይ ስላለን ሁሉም እንደየመክሊቱ እውነታውን በማውጣት መረባረብ አለበት ሲሉ በአንክሮ አሳስበዋል:: የውጭ ጉዳይ ቃል አቀባይ አምባሳደር ዲና ሙፍቲ ምራባውያን ለኛ ያገዙ በመምሰል ከጎረቤት አገራት ጋር እንድንወዳጅ አማራጮችንና ምክረ ሀሳቦችን ያቀርባሉ እውነታው ግን ሌላ ተቃርኖ ስለኖነ ምሁራኑ ከመማር ማስተማሩ ባሻገር በዲፕሎማሲው ዙሪያ ሰፊ ስራ በመስራት ማገዝ እንዳለባቸው አሳስበው ከመንግስት ብቻ ያለው የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ አዋጭ አለመሆኑን አስገንዝበዋል:: አምባሳደሩ በማስከተል አገርን የማዳን ስራ የምንሰራበት ወቅት አሁን ስለሆነ በውጭ አገር ያሉት ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የጀመሩትን የ “በቃ” ዘመቻ ማስፋፋት እንደሚገባ ተናግረዋል:: መድረኩም በዚህ የሚያበቃ ሳይሆን ለወደፊት የውጭ ጉዳይ ሚኒስተር መስሪያ ቤቱ በእቅድ ይዞ ሌሎች መድረኮችንም መፍጠር እንደሚቻል አምባሳደሩ ገልፀዋል:: በተጋባዥ እንግድነት የተገኙት የሰብአዊ መብት ተሚጋች

ወደ ገፅ 5 ዞሯል



## ሠሞነኛ

ይህ አምድ ከዜናዎች በተጨማሪ ወቅታዊ ጉዳዮችን መነሻ በማድረግ ሀተታዊ ፅሁፎች ይቀርብበታል



የኢፌድሪ ትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ አመራሮችና መምህራን ጋር በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ጥበብ ህንፃ አዳራሽ በትምህርት ጥራት ላይ ያተኮረ ውይይት ሲያካሂዱ

# 'የትምህርት ጥራት መውደቅና ለውድቀቱ ባለቤት ማጣት'

በሙሉጎጃም አንዱዓለም

የኢፌድሪ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ አመራሮችና መምህራን እንዲሁም የአስተዳደር ሠራተኞች ጋር የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል በቀጣይ አምስት ዓመታት ውስጥ መሠራት ባለባቸው ጉዳዮች ዙሪያ የውይይት መድረክ ማካሄዳቸው ይታወሳል፡፡

ውይይቱን በበላይነት የመሩት ሚኒስትሩና የትምህርት ሚኒስቴር ከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኢታ ዶ/ር ሳሙኤል ክፍሌ፣ አጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኢታ ዶ/ር ፋንታ ማንደፍሮ ከዩኒቨርሲቲው ፕሬዘዳንት ዶ/ር ፍሪው ተገኘ ጋር በመሆን ነው፡፡

በውይየቱ ከመምህራን ደመወዝና ጥቅማጥቅም፣ ከትምህርት ፖሊሲና ትምህርት ተቋማት መሪዎች አቅም ጋር በተያያዘ ያለው ሃገራዊ ጉዳይ ለትምህርት ጥራት መውደቅ መንስኤ እንደሆነ በሰፊው ተነስቷል

የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትም ሆነ አጠቃላይ የትምሀርት ዘርፍ ከፖለቲካ፣ከዘረኝነትናከጠባብ አመለካከት መለየት እንደሚገባ በአፅንኦት ተጠቁሞ ከትምህርት ጥራት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት በተነሱ የመፍትሄ ሀሳቦች ዙሪያ ሰፋ ያለ ውይይት ተካሂዷል፡፡

ለትምህርት ጥራት መሻሻል አንዱ በሌላው ላይ እጅ መጠቆሙን ትቶ ሁሉም ይመለከተኛል በሚል መንፈስ በጋራ መስራት ያስፈልጋል ተብሏል፡፡

ምክንያቱም ችግሩ የት ላይ ነው ብሎ ለመለየት ሲሞከር ከታች ክፍል ያሉ ተማሪዎች ለምን ደካማ ሆኑ ሲባል ከዩኒቨርሲቲ የሚወጡ መምህራን ችግር ነው ይባላል፣ዩኒቨርሲቲ የሚገቡት ተማሪዎችስ ለምን ደካማ ሆኑ ሲባል ከታች ክፍል ተገፍተው ስለሚመጡ ነው እየተባለ ችግሩ እንኳ ባለቤት አጥቷል ብለዋል የትምህርት ሚኒስተሩ ፕሮፌሰር ብርሀኑ፡፡

እንደዛሬው አያድርገውና ይላሉ ሚኒስትሩ በቀድሞ ግዜ፡-

"መሸሪት ኩሪ ኩሪ
ሊወስድሽ መጣ አስተማሪ"

ይባል ነበር በማለት በቀደመው ጊዜ መምህራን በማህበረሰቡ ዘንድ የነበራቸውን ክብር አንስተው አሁንም የነበረውን ክብርና ተቀባይነት የሚያኮራ ስራ በመስራት የመምህንን ክብር ለመመለስ ቁርጠኝነት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

የችግሩን ፈርጀ ብዙነት የሚያነሱ እና በየደረጃው ያሉ ችግሮችን የሚጠቁሙውይይቶች ከተካሄደ በኋላ ከታዳሚዎችና ከመድረኩየሚከተሉት የመፍትሄ ሃሳቦች ተጠቁመዋል፡-

1. ትምህርትን ከፖለቲካ፣ከዘረኝነት/ከጎጠኝነት/ከብሄርተኝነት መነጠል፤
2. ሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች የፌደራል ተቋም እንጂ የአንድ አካባቢ ማህበረሰብ ስባስብ አለማድረግ፤
3. ከአመራሩ ጀምሮ ከሰራተኛው እስከ ተማሪው የሁሉም ብሔር ስብጥር ሆኖ ያለምንም ልዩነት መማር ማስተማሩን ማሳለጥ፤
4. ካሪኩለምሲዘጋጅበደቦሳይሆን በስርዓት በጉዳዩ ባለቤት ቢሆን፤
5. የኩረጃስርዓት እንዲነጥፍማድረግ፤
6. የከፍተኛትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ምደባ አገር አቀፍ ወጥ የሆነ አሰራር እንዲኖረውማድረግ

7.የዩኒቨርሲቲመምህራንአስፈላጊው ክብርና ጥቅማጥቅም ተሠጥቶት በሙሉ አቅሙ እንዲሰራ ማድረግ፤

8. በሰሜስተርና በዓመቱ ውስጥ የትምህርት ሰዓት ሳይሸራረፍበአግባቡ ተማሪዎች እንዲማሩ ቢደረግ

ሚኒስትሩበማጠቃለያቸው ለወደፊት የትምህርት ዘርፉን ለማሻሻል የመምህራንና የትምህርት ማህበረሰቡ ተሳትፎ ቀጣይነት ያለው ሃገራዊ ምክክር ማካሄድ ተገቢ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

ሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ለፖሊሲ ማሻሻያነት የሚውሉ ሃሳቦችንግብዓትበመለገስረገድ ትኩረት እንዲሰጡ በመግለጽ የመምህራንጥቅማጥቅምንና ተያያዥ ጉዳዮችን ለማስተካከል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እንደሚመክሩበት ተናግረዋል፡፡

## ወቅቱን የዋጀ ... ከገፅ 3 የቀጠለ

የክብር ዶ/ር ኦባንግ ሜቶ ከውጭም ከውስጥምኢትዮጵያን ሊከፋፍሏት ያሰፈሰፉ ጠላቶች ከፍተኛ ጫና እያሳደሩ መሆኑን በአንክሮ ተናግረው ይህችን የረጅም ዓመት ታሪክ ያላትን አገር ለማዳን ሁሉም መረባረብ እንዳለበትና የ"በቃ" ዘመቻው መስፋፋት እንዳለበት ገልፀዋል፡፡

የባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ ወቅቱን የዋጀ መድረክ በማዘጋጀት የአንበሳውን ድርሻ በመውሰዱ በማመስገን ይበል የሚያሰኝ ስራ ነው ብለዋል፡፡

በተጨማሪም ሁሉም ማህበረሰብ የተደቀነብንን ፈተና ለመወጣት በእውቀትና በጥበብ አገርን የማዳን ስራው ተጠናክሮ እንዲቀጥል የክብር ዶክተር ኦባንግ ተናግረዋል፡፡

በመርሀ ግብሩ ዶ/ር አልማው ክፍሌ "የዘመናዊቷ ኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ጠቅላላ ሁኔታ፣ ስኬቶችና ተግዳሮቶች ከ1847/8-2014 ዓ.ም"፤ዲፕሎማት አቶ ዘሪሁን አበበ "አሁናዊ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ"፤የባ ሕ ር ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነትና ተግባቦትተባባሪ ፕሮፌሰር ዶ/ር አደም ጫኔ "የም ዕ ራቡ ዓለም ሚዲያዎች፤ የአፍሪካ ገፅታ እና በዲፕሎማሲ ላይ ያሳደሩት ተፅዕኖ፤ የሰብአዊ መብት ከፍተኛ ኤክስፐርት ዶ/ር ዘላለም ሞገሴ በበይነ መረብ ታግዘው ከታንዛንያ "የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ በጦርነት ወቅት፡- ድክመቶ፣ ጥንካሬዎችና የወደፊት ቀጣይ አቅጣጫዎች" በተሰኙ ርዕሰ ጉዳዮች ጥናታዊ ፅሁፎች እና መወያያ ፅሁፎች አቅርበው በታዳሚዎች ሰፋ ያለ ውይይት ተካሂዷል፡፡

# 'እውቀትን በተግባር'


በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የባሕር ዳር ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የሜካኒካል እና ኢንዱስትሪያል ምህንድስና ፋኩልቲ መምህራንና ቴክኒካል ረዳቶች የበቆሎ መፈልፈያ ማሽኖችን ሰርተው ሙከራ አደረጉ::

በጦርነቱ ምክንያት የሚከሰተውን የምርት ብክነት ለመቀነስ በተቋሙ ከሚንቀሳቀሱ ቡድኖች መካከል ለአግሮ ሜካናይዜሽን ስራወች የሚያገለግሉ ማሽኖችን እየሰራ ያለው የሜካኒካልና ኢንዱስትሪያል ፋኩልቲ ባልደረቦችን የያዘው ቡድን ይገኝበታል፡፡

ይህ ቡድን ታኅሣሥ 23/2014 ዓ.ም በባሕር ዳር ዙሪያ ወረዳ ወረብ ቀበሌ ተገኝቶ የሰራውን የበቆሎ መፈልፈያ ማሽን ሙከራ አድርጓል፡፡

በሜካኒካል እና ኢንዱስትሪያል ምህንድስና ፋኩልቲ መምህርና የበቆሎ መፈልፈያ ማሽን አምራች ቡድን አስተባባሪ የሆኑት ዶ/ር ጌታ ኪ/ማርያም እንደገለጹት አራት አይነት የተለያዩ ማሽኖችን ማምረታቸውን ጠቅሰዋል፡፡ በዕለቱ ከ19 ኩንታል በላይ በቆሎ በማሽን የተፈለፈለላቸው አርሶ አደር አቶ ቻሌ አዲሱ በተደረገላቸው በጎ አድራጎት የባሕር ዳር ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩትን አመስግነው ዩኒቨርሲቲው ከአሁን በፊትም ብዙ ነገሮችን ረድቶናል፤ ወደፊትም ትብብራችሁ አይለየን፤ በማለት ደስታቸውን ገልጸዋል፡፡

በሌላ መልኩ የወረብ ቀበሌ የሰብል ልማት ባለሙያ የሆኑት አቶ አንላይ ዳኘው ቴክኖሎጂው በጣም የተሻለ ቴክኖሎጂ መሆኑን፣ በጣም ፈጣን መሆኑንና የተሻለ የነዳጅ አጠቃቀም ማየታቸውን ተናግረዋል፡፡ በመጨረሻም ዶ/ር ጌታ ኪ/ማርያም ለአሥር የአርሶ አደር ቤተሰቦች በእጅ የሚያዝ የበቆሎ መፈልፈያ ማበርከታቸውን ገልፀው ይህን ቴክኖሎጂ በስፋት ወደ አርሶ አደሩ ለማሰራጨት በቂ ግባት ሰብስበናል ብለዋል፡፡



በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የባሕር ዳር ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የሜካኒካል እና ኢንዱስትሪያል ምህንድስና ፋኩልቲ መምህራንና ቴክኒካል ረዳቶች የበቆሎ መፈልፈያ ማሽን በሙከራ ላይ

## University-Industry Linkage... continued from page 14

users who can then further deand exploit the technology into new products, processes, applications, materials or services. It is closely related to (and may be considered a subset of) knowledge transfer. By transferring technologies, we can bring positive impact to the society.

Our office follows two approaches regarding technology transfer projects:

i. Announcing call for proposals on yearly bases after identifying thematic areas (such as Energy, Agricultural mechanization, Health, Waste management, System development, Post-harvest technology, etc.)
ii. Identifying specific problems and announcing calls for technology proposals which can solve the problems

### University- Industry Linkage

Here it is worth defining what Industry means first…! Most of us think of industry as large-scale manufacturing of goods in well-organized plants with a high degree of automation and specialization. Although this is a common example of industry, it can also include other commercial activities that provide goods and services such as agriculture, transportation, hospitality, and many others.

Industry is actually classified into different categories or levels. Many authors classify industry into five levels.

**Primary industries:**

Industries that extract or produce raw materials from which useful items can be made. Example- Mining activities, forestry, fishing, agriculture, etc Secondary industries: Industries that change raw materials into usable products through processing and manufacturing.

**Tertiary industries:**

Industries that provide essential services and support to allow other levels of industry to function. They are often called service industries and this level includes transportation, finance, utilities, education, retail, housing, medical, and other services.

**Quaternary industries:**

Industries meant for the creation and transfer of information, including research and training. They are often called information industries. Quinary industries: Industries that control the industrial and government decision-making processes.


### What is University-Industry Linkage (UIL) then ?

By its definition University- Industry Linkage is the process of deploying sustainable relations with universities, industries (which can be of business, education, manufacturing, service etc as elaborated above), research institutions and TVETs on the basis of principled and transparent negotiations and agreements for realizing mutual benefits. UIL is actually a necessary condition to transfer knowledge and/or technology from university to the industry and vice versa. A meaningful collaboration between universities and industries could provide a variety of benefits for both parties.

Bahir Dar University through its various colleges/faculties/institutes/schools can create links with industries/institutions in many ways: conducting collaborative research; providing consultancy services; patent licensing; providing tailored short term trainings; curriculum development; construction supervision, design verification, enterprise support and development, student internship and staff externship programs.

Dear reader, in which category Does your respective industry belongs to then to link with?
For further information, contact us:
@Wisdom Tower, First floor, office number 110
Bahir Dar University
Vice President for Research & Community Services
Office of Technology Transfer and University-Industry Linkage
Tel: +251583206014

**CONGRATULATIONS! BIT IS ONE OF THE TWO AFRICAN MEMBERS OF GLOBAL COUNCIL FOR SCIENCE AND ENVIRONMENT (GCSE) AS OF 3/29/2021.**



## እጅ-ከምን

በዚህ አምድ የዩኒቨርሲቲው ባልደረቦች እጅ ከምን ስንል አለን የምትሉት ለአንባቢ የሚበቃ ፅሁፍ ይስተናገድበታል

# “ህዝቡ በባዶ እጁ ከስናይፐር ጋር ተናንቆ ያመጣው ድል በሌሎች ድክመት ለፍሬ ካልበቃ...”

በሙሉጌታ ዘለቀ

በወቅታዊ የሀገራችን ጉዳይ ምክንያት በተከሰተው ጦርነት እና ተያያዥ ችግሮች ዙሪያ የምሁራን ሚና ምን መሆን አለበት? በሚለው ሀሳብ ላይ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ህክምና እና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የአዕምሮ ጤና ሕክምና ኢፒዲሞሎጅስት እና በማህበረሰብ ጤና ት/ቤት መምህርና ተመራማሪ ከሆኑት ፕሮፌሰር ፈንቴ አምባው ጋር ቆይታ አድርገናል።

ፕሮፌሰር ፈንቴ የተከሰተው አገራዊ ችግር በሚገባ ካላጤነው ችግሩን ለመረዳትም ሆነ ለመፍታት አዳጋች ይሆናል ይላሉ::

እንደሚታወቀው ጦርነቱ የተካሄደው ህውሀት ኢሀዴግ ሃገራችን በአግባቡ መምራት አቅቶት በህዝብ ግፊት ከለቀቀ በኋላ በወንጀል ተከሶ እንዲቀርብ ሲፈለግ ሌላ ተጨማሪ ወንጀል ፈጽሞ አሸባሪ ተብሎ በተፈረጀ ሀይል እና ከስልጣን እንዲወርድ ግፊት በፈጠረበት ህዝብ እንዲሁም ህዝቡ በመረጠው አዲስ መንግስት መካከል ነው::

ህዝቡ ይህ አሸባሪ ተብሎ የተፈረጀን ሀይል ከስልጣን እንዲወርድ ለማድረግ ሲነሳ ከቆራጥነቱ እና እጅግ ጥቂት ከሚባሉ ጥይት አልባ ኋላ ቀር የጦር መሳሪያዎች ውጭ ምንም አልነበረውም:: ይህም ሆኖ ኢትዮጵያን እናፈርሳታለን ብሎ ከተነሳ ሀይል እናንተ ትፈርሳላችሁ እንጅ ኢትዮጵያ አትፈርስም ብሎ የተጋፈጠ ጀግና ህዝብ ነው:: ስለዚህ ከስነ-ልቦና አንጻር ድል እንጅ ኪሳራ አልነበረም:: በመጀመሪያው ዙር ላይ ስነ-ልቦናው ከፍተኛ የድል አድራጊነት ስሜት ነበረው::

ይህ አሸባሪ እና አውዳሚ ሀይል በተጠና እና እጅግ በተጠናከረ ሁኔታ በሰሜን ህዝብ ላይ ጥቃት ፈጽሞ ሥልጣን ለመቆጣጠር ሲሞክር ህዝቡ ከአዲሱ መንግስት ጋር እጅና ጓንት ሆኖ የራሱን አደረጃጀት በመጠቀም ከፍተኛ ገድል ሰርቶ የማይረሳ ሁለንተናዊ ድል ነው ያስመዘገበው ይህንን በደንብ መገንዘብ ያስፈልጋል::

ኢትዮጵያን ለማፍረስ ጦር አደራጅተው ከመጡት ሀይሎች የተወሰኑት ተገደሉ ግማሾች ተያዙ ቀሪዎች ተንቤን በርሃ ገቡ:: ይህ ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ ሥነልቦናን የሚገነባ እንጅ የስነልቦና ጫና የሚፈጥር አይደለም::

ከሰሜን እዝ ቅጣት በኃላ ቀጥሎ የተከሰተው ትግል ህዝቡ ባልጠበቀው መንገድ ጦርነቱ ከትግራይ ወጥቶ በአማራና በአፋር ክልሎች እንዲሆን ሲደረግ መንግስት ምክንያቱን ለመግለጽ እና ህዝቡን ለማስረዳት ሞክሯል::

ለጊዜው መንግስት በአሸባሪው ሀይል ፕሮፖጋንዳ ተበልጦ ስለነበር ህዝቡ የስነ-ልቦና ጫና እና መደናገር ደረሰበት:: መንግስትና ህዝብን ከድተው ከጠላት ጋር ወግነዋል የተባሉ አንዳንድ ባለስልጣናት አሉ የሚባል ወሬ በከፍተኛ ደረጃ ተናፈሰ በገንዘብ የሚገዙ የጦር መኮነኖች ወ.ዘ.ተ አሉ የሚባል ወሬ ማናፈስ ጀመረ የውጭ ሃገር መንግስታት ለጠላት ማገዝ ጀመሩ::

ተቀበሩ የተባሉ ከባድ መሳሪያዎች አሉ መባሉ በማህበረሰባችን ውስጥ የሚኖሩ አንዳንድ ሰዎች እንዲያውም ብዙ ሰዎች ማለት ይቀላል በብሔር ትስስር ለጠላት መስራታቸው እየታወቀ መጣ:: ያለብርቱ ጦርነት ቦታዎች በጠላት ሲያዙ ቻሉ ለምሳሌ ወልደያን መጥቀስ ይቻላል:: ህዝቡ ግራ ተጋብቶ ነበር ግራ መጋባት ነው እንጅ የስነ-ልቦና መውረድ አይደለም::

በአንጻሩ ጠላት የጦርነቱን አውድማ አማራና አፋር ክልል ሲሆን እንደልቡ መፈንጨት ጀመረ:: ማረድ መብላት የፈለገውን መግደል የፈለገውን ማድረግ መድፈር ጀመረ:: ይህም ሆን ብሎ ስነ-ልቦናን ዝቅ ለማድረግ መመገቢያ ሰሃን ላይ ሁሉ ሳይቀር መፀዳዳት ጀመረ ሰራዊቱና ፋኖ ባሸነፈው ቁጥር በጅምላ ንፁሀንን መግደል ጀመረ አላማው በቀጥታ ስነ-ልቦና ላይ ያነጣጠረ ነበር::

እውነቱን ለመናገር ጠላት እንዳሰበው ጊዜያዊ ድል አግኝቶበት ነበር::

በከፍተኛ ደረጃ የህብረተሰባችን ሞራል ወርዶ ነበር:: ይሁን እንጅ ብዙም ሳይቆይ መንግስት ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል እንዲንቀሰቀስ እና ወደ ግንባር እንዲሄድ ጥሪ አደረገ

ህዝቡ አንድ ባንድ ነቅሎ ወጣ እንዲያውም እኔ በጣም በትክክል እንደማስታውሰው እና እንዳየሁት በጉጉትና በወኔ መትመም ጀመረ::

የሰዎች የድል አፈጻጸም ማንነታቸው መታየት ሲጀምር የህዝቡ ሥነ-ልቦና እንደገና ከፍ አለ:: በቆራጥነት የሚዋጉ መሪዎችን ሲያይ የተዋጊነት መንፈሱ ተቀሰቀሰ አሸናፊነትም አይቀሬ መሆኑን አመነ ይህም ለስነልቦና ማደግ ትልቅ ነገር ነው::

ህዝቡ እራሱ ገድል እየሰራ መትረጊስና ብሬን እየማረከ ታጠቀ በባዶ እጅ ገጥሞ መሳሪያ በእጁ ያዘ አሁናዊ ስነ-ልቦናው ይህ ነው::

አሁን ያለንበት የወገን/የህዝብ የስነ-ልቦና ከፍታ ነው:: ሁሉም ቦታ ላይ በምሳሌ ሊጠቀሱ የሚችሉ እሚገራርሙ አገላለጾችን ሰምተናል::

ስለዚህ አሁን ያለው የአሸናፊነትስነ-ልቦና ነው:: በሌላ መልኩ ደግሞ ንብረትን ማውደማቸው የወገኖቼ ሞት፣ መዘረፍ፣ አካል መጉደል እና መደፈር የደረሰባቸው የእምነት ተቋማት ጥቃት በምድር ላይ አሸባሪው ሀይል እስካለ ድረስ ምንም አይነት መደምሰስ ቢደርስበት ርዝራዡ ባደረሰው በደል ተመጣጣኝ ቅጣት አይደለም ብሎ ስለሚያምን አሁንም ቁጭት አለው ይህ የስነ-ልቦና ሥብራት ሊባል አይችልም::

ስለዚህ እንደብሔር ጫናዎች ቢኖሩም ባባቶቹ ስነ-ልቦና ከፍታ ላይ የሚገኝ ማህበረሰብ ነው:: በህይወት ማጣት ማዘን፣ የንብረት መወደም እና በስነ-ልቦና መሰበር የተለያዩ ነገሮች ናቸው:: ማዘን ምንጊዜም ያለ ነው በስነ-ልቦና ግን በአባቶቹ የወጣ ህዝብ ነው::

በቡድን ደረጃ የስነ-ልቦና ጫና የለም:: የተጎዱ ያዘኑ ቤተሰቦች አሉ በነሱ ላይ ሥነ-ልቦናዊ ችግሮች አሉ ለምሳሌ በማን ላይ እንደተከሰተ እና እንዴት መታከም እንዳለበት ለውሳኔ በሚመች መልኩ ማጠናከር እና መፍትሄ እንዲያገኙ ጥብቅና መቆምን ያካተተ በዋናነት ደግሞ የሚከናወኑ ተግባራት ሲስተምንየሚያጠናክሩ እና የተቀናጁ

"ኢህአዲግ ካደረሰው ጉዳት ዋናው የተበላሸ አሰራር ባህል ማድረጉ ነው። ... ይህንን የሚታገል ከምሁራን መካከል ፋኖ ያስፈልጋል። ... ህዝቡ በባዶ እጁ ከስናይፔር ጋር ተናንቆ ያመጣውን ድል በሌሎች ድክመት ለፍሬ ካልበቃ የስነ-ልቦና ሥብራቱ ለክፍለ ዘመን ሊያስነክስ ይችላል።ለጥገናም የሚያስቸግር ይሆናል። "

ፕሮፌሰር ፈንቴ አምባው በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ህክምና እና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ

ወደ ገፅ 12 ዞሯል

# ባህረ-ሃሳብ

ይህ አምድ የተለያዩ የሀሳብ ልዩነቶችን የሚያንፀባርቁ ፅሁፎች፣ ትዝብቶች እና ክርክሮች ይቀርብበታል

## ያለምሁራን ተሳትፎ... ከገፅ 15 የቀጠለ

ናይል፡- መምህራንየእድገት መሰላሎች ተጠቃሚ ናቸው ወይ?

አቶ ፈለቀ፡- የመምህራንን የደረጃ እድገት እና የጎንዮሽ ተጠቃሚነት በተመለከተ ያለውን ሁኔታ በየፈርጁ ስንመለከት፡-

1ኛ. የደረጃ እድገት ኬሬር ስትራክቸርን ለዩኒቨርሲቲ ምሁራን መንግስት ባለመፍቀዱ፤ አስር አመትና ከዚያ በላይ ያስተማረ የዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ ምሁር እሱ አስተምሮ ካስመረቀው የትላንት ተማሪው እኩልናአንዳንዴምያነሰክፍያመፈጸሙተገቢነትየለውም።

አውሮፓውያን እንደሚሉት የስራ ልምድ ትልቅ ቤተ-ሙከራ ነው የሚለውን መርህ በመከተል ተጠቃሚነታቸው የሚረጋገጥበት ስርአትንመዘርጋት ያስፈልጋል። ለምሳሌ ከ1ኛ-12ኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን የኬሬር ስትራክቸር ስርአት ተጠቃሚ ሲሆኑ የሀገሪቱ የመጨረሻ የእውቀት ጓዳ ማፍለቂያው ዩኒቨርሲቲ መምህራን ግን የስርአቱ ተጠቃሚ አይደሉም።

2ኛ.ታክስበአፍሪካዩኒቨርሲቲዎችበአብዛኛውየመምህራንን ደመወዝ ከታክስ ነጻ አድርገው የመክፈል ሁኔታ አለ። በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ግን የደመወዝ 35 በመቶ ታክስ መደረጉ ተገቢነት የለውም ስለዚህ በልዩ ሁኔታ ታክስ ከ35 በመቶ በታች ሲሆን ይገባል።

በተያያዘም ደመወዝ ከተከፈለ በኋላ በተጨማሪ ከመደበኛ እና ኤክስቴንሽን፤ የርቀት ትምህርት፤ የክረምት ትምህርት፤ ፈተና ማዘጋጀትና በማረም ሂደት፤ተጋባዥ እንግዳ ሆኖ በማስተማር፤ተማሪዎችን በሪሰርች በማማከር የተማሪዎችን የምርምር ውጤት ለመገምገምና ለመፈተን ወዘተ. በመሳሰሉት የስሯቸው ስራዎች ግብር ከተከፈለበት ላይ ከደመወዝ ጋር ተጨምሮ የሚገኘው ገንዘብ 35 በመቶ መቆረጡ በየትኛውም መመዘኛና መለኪያ ተቀባይነት ስለሌለው እና የሌሎች ሀገሮችም ተሞክሮ ስለሌለ ገንዘብ ሚኒስቴርና ገቢዎች ሚኒስቴር ከታክስ ነጻ እንዲያደርጉ በጥናት የተደገፈ ጥያቄ ይቀርባል።

3ኛ. የመምህራን የመኖሪያ ቤት ጉዳይ መጠለያ ለሰው ልጆች አንዱ መሰረታዊ ፍላጎትና ተረጋግተው ስራቸውን ለማከናወንና ብቁ ዜጋ ለማፍራት እንዲችሉ ከፍተኛ ሚናን ይጫወታል።

ይሁን እንጅ ለዩኒቨርሲቲ መምህራን በአብዛኛው የቤት ችግር በመኖሩ ተረጋግተው ስራቸውን ለመስራት እየተቸገሩ ይገኛሉ። ስለሆነም ቤት መስሪያ ቦታና የብድር አቅርቦት እንዲመቻች፤ነጻ የህክምና አገልግሎት እንዲመቻች፤ የዩኒቨርሲቲ መምህራንና ቤተሰቦቻቸው የነጻ ህክምና አገልግሎት እንደሌሎች የልማት ድርጅቶች የህግ ማዕቀፍ ኖሮት ስራ ላይ እንዲውል ሊደረግ ይገባል።




4ኛ.የብድር አገልግሎት የኢትዮጵያ አየር ንገድ፤ባንኮች፤ጉምሩክ፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፤ገቢዎች ወዘተ የመሳሰሉት ተቋማት በረጅም ጊዜ ክፍያ በትንሽ ወለድ የብድር አገልግሎት ተመቻችቶላቸው መኪና ከቀረጥ ነጻ ያስገባሉ፤ የቤት መስሪያ ብድርም ይመቻችላቸዋል። ስለሆነም ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራንም እንደሌሎቹ የልማት ድርጅቶች በተመሳሳይ ሊፈቀድ ይገባል።

5ኛ. የጎንዮሽ ክፍያ የመምህራን የማበረታቻና ጥቅማ ጥቅም ክፍያ በሌሎች የልማት ድርጅቶች እንዳለው የሙያ አበል ክፍያ፤የስልክ ካርድ፤ የትራንስፖርት አበል፤ የጤና ኢንሹራንሽስ እና የህይወት መድህን ዋስትና እንዲፈቀድ በጥናቱ ተመላክቷል። በአጠቃላይ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት የመምህራን ክብርና የጥቅማ ጥቅም ጥያቄዎች የፌደራል መንግስት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ለሀገር እድገት ዋልታና ማገር ለሆነው የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ምላሽ በመስጠት ምሁራን በአገር ግንባታ ላይ የበኩላቸውን አስተዋጾ እንዲያደርጉ ማድረግ ያስፈልጋል፤

ናይል፡- ስለቃለ-ምልልሱ እጅግ አድርገን እናመሰግናለን።

አቶ ፈለቀ፡- እኔም አመሰግናለሁ!

# ደቀመዛሙርት

ይህ አምድ በዋነኛነት የተማሪዎች ድምፅ እና ተማሪነትን የሚመለከቱ ፅሁፎች ይቀርብበታል

## በህልውና ዘመቻው የተማሪዎች ተሳትፎ

በሙሉጎጃም አንዱዓለም

አሸባሪው የትግራይ ወራሪ ኃይል በአማራ እና በአፋር ክል ሎች በከፈተው አስከፊ ጦርነት ምክንያት በአመዛኙ የአገሪቱ የሰሜኑ ክፍል በጦርነት ሲናጥ፣ ኗሪዎች ከቀያቸው ተፈናቅለው፣ ቤት ንብረታቸው በወራሪው ኃይል ተዘርፎ፣የቀረውም ወድሞ፣ ምንም የማይናገሩት እንስሳት እንኳ ሳይቀሩ በግፍ ተገድለው፣ የዕድሜ ገደብ ሳይኖር ዓለም በቃኝ ብለው የመነኮሱት ሳይቀሩ ከህፃን እስከ አዛውንት በአደባባይ አንድን ሴት ለአምስት፣ ለስድስት፣ ለሰባትም.. እየደፈሩ ባሉበት ወቅት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ይህን ሁሉ ጉድ እያዩ መማር ባለመቻላቸው ከተማሪዎች መማክርት ጋር የዩኒቨርሲቲው አመራሮች መክረው ሁሉም ተማሪዎች ከዩኒቨርሲቲ ወጥተው ለህልውና ዘመቻው አቅማቸው በፈቀደው መጠን ለመሳተፍ ትምህርታቸውን ማቋረጣቸው ይታወሳል፡፡

ዩኒቨርሲቲውን ለቀው ከወጡ በኋላ በምን ተግባር እንደተሰማሩ ዳሰሳ ስናካሂድ እንደማንኛውም ሰው ለመከላከያ፣ለልዩ ኃይል፣ ለፋኖና ለሚሻ ለሚዘጋጀው የስንቅ ዝግጅት በማገዝ፣በሰብል ስብሰባ ስራ በመሰማራት እንዲሁም የማህበረሰብ ማንቃት ስራ ላይ ላቅ ያለ ተሳትፎ እንደነበራቸው ተገንዝበናል፡፡

ቁጥራቸውን በውል ማወቅ ባንችልም ግንባር ድረስ በመዝመት በጦርነቱ የተሳተፉ እንዳሉም መረጃው ደርሶናል፡፡

በሌላ መልኩ ጦርነቱ ከሚካሄድበት አካባቢ የመጡ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችየቤተሰቦቻቸውንደህንነት ለማወቅ የተቸገሩና መሄጃው ግራ የገባቸው የአብነት ትምህርት ቤት የገቡና ቤተክርስቲያንተጠልለው ያ ሉ ተ ማ ሪ ዎ ች ም እ ን ደ ነ በ ሩ አ ስ ተ ው ለ ና ል ፡ ፡ የአማራ ተማሪዎች ማህበር (አተማ) በሚል ስያሜ ከተለያዩ የአማራዩኒቨርሲቲዎች የተውጣጡ ተማሪዎች ስብስብ ሲሆን ለህልውና ዘመቻው የተለያዩ ስራዎችን ለማከናወን ያመች ዘንድ ፔዳ ግቢ እንዲቆዩ ተፈቅዶላቸው ዘርፈ ብዙ ተግባራትን እያከናወኑ መቆየታቸውንም አስተውለናል፡፡

ውድ አንባቢያን ለዛሬ የማህበሩና የባህር ዳር ቅርንጫፍ ሊቀመንበር ተወልደ በጋሻው በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ኤሌክትሪካል ምህንድስና የሶስተኛ ዓመት ተማሪ ማህበሩ በህልውና ዘመቻው የተሳተፈባቸውን ተግባራት እንዲያጋራን ጋብዘነው አጠር ያለ ቆይታ አድርገናል፡፡ በወቅቱ ከዩኒቨርሲቲው ለመውጣት ሲወሰን ደስተኛ ነበርኩ ይላል ተማሪ ተወልደ ሀገር እየተወረረች፣ህዝብ በግፍ አካባቢውን ለቆ እየተሰደደ፣ እየታረደ ባለበት ወቅት በግሌ ትምህርት የምማርበት አቅምም፣ ስሜትም፣ፍላጎትም፣ አልነበረኝም ብሏል ምክንያቱን ሲገልፅ፡፡ ዩኒቨርስቲውን ለቆ እንደወጣ ወደ ትውልድ ቦታው ሄዶ ወረዳ ላይ ወጣቱን የማንቃት ስራዎችን፣ማህበረሰቡ የተረጋጋ ስነ-ልቦና እንዲኖረው፣እንዲሁም አቅሙ በፈቀደው መጠን በአካባቢው የሚኖሩ ባንዳዎችን በማጥናት መሳተፉን ተናግሯል፡፡

ከተወሰነ ቆይታ በኋላ የአማራ ተማሪዎች ማህበር (አተማ) የባህር ዳር ቅርንጫፍ የራሱን ግብረ ሀይል አደራጅቶ ስራ ሲጀምር ወደ ባህርዳር መጥቶ ማህበረሰቡን የማንቃትና ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ፣የደም ልገሳ ፕሮግራሞችን ማስተባባር እንዲሁም ተማሪዎችን ትምህርት ቤቶች ድረስ በመውሰድ በአማራ ህዝብ ላይ የተሠራብን ግፍ በጥልቀት እንዲረዱ እና መሠል ድርጊቶች ዳግም እንዳይከሰቱ ለማድረግ ተማሪዎቹ ጉልህ ሚና እንዳላቸው ግንዛቤ የማስጨበጥስራ መስራቱን ገልጿል፡፡

የማህበሩ አባላት በርካታ የመድረክ ፕሮግራሞችን እሰከ ወረዳ ድረስ ወርደው ለመስራት ቢያቅዱም በተለያዩ ተፈጥሯዊ ፣ማህበራዊና ፖለቲካዊ (ቢሮክራሲ) እንቅፋት እንደሆኗቸው ተናግሯል ፡፡ ለወደፊትም አጠቃላይ በጦርነቱ ምክንያት የወደሙ ንብረቶችን፣ ሰባዊ ቀውሶች እና ተጓዳኝ ውድመቶችን ለታሪክ ሰንዶ ለማስቀመጥ እየተጠኑ ያሉ ስራዎች መኖራቸውን ገልፆልናል፡፡

በዚህ ወቅት የጋራ ለሆነው ጉዳይ በአንድ መንገድ በመሄድ፣ የፖለቲካ ልዩነትን ወደ ጉን በመተው በተናጥል ከማሰብ በጋራ እና በአድነት አገራችን በአሸንፊነቷ እንድትቀጥል ተማሪዎች ከፍተኛ ሚና ስለሚጫወቱ ትምህርታቸውን በአግባቡ ተረጋግተው በመማር የለውጡን ጉዞ ማሳለጥ እ ን ደ ሚ ጠ በ ቅ ባ ቸ ው መ ል ዕ ክ ት አስተላልፏል፡፡

ውድ አንባቢያን በቀጣዩ እትማችን የሌሎችን ተማሪዎች መልካም ተሞክሮ የምናስቃኛችሁ መሆኑን ለመግለፅ እንወዳለን፡፡

> ሀገር እየተወረረች፣ህዝብ በግፍ አካባቢውን ለቆ እየተሰደደ፣ እየታረደ ባለበት ወቅት በግሌ ትምህርት የምማርበት አቅምም፣ ስሜትም፣ፍላጎትም፣ አልነበረኝም
>
> ተወልደ በጋሻው በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ኤሌክትሪካል ምህንድስና የሶስተኛ ዓመት ተማሪ

## የዐይን ጤናን ለመጠበቅ...

ከገፅ 10 የቀጠለ

ያባብሰዋል፡፡

በአጠቃላይ በኮምፒዩተር መጠቀም ምክንያት የሚከሰተዉ የዓይን ጤና መታወክ ችግር ጊዜያዊና ቋሚ ጉዳት የማያስከትል ነዉ፡፡ ብዙ ሰዓት ኮምፒዩተር ላይ ማሳለፍ የግድ ከሆነ ተገቢዉን ጥንቃቄዎች በማድረግ የሚፈጠሩ የዓይን ስሜቶችን መከላከልና መቀነስ ይቻላል፡፡

ሠ. መደበኛ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ

ዓይናችን ጤናማ ሆኖ ለመቆየትና ሥራዉን በተገቢዉ ሁኔታ ለማከናወን ከፍተኛ የኦክስጅን መጠን ያስፈልገዋል፡፡ ስለሆነም በደም ዉስጥ የሚገኘዉን የኦክስጅን መጠን የሚጨምር የአካል ብቃት እንቅስቃሴ (በእንግሊዝኛዉ አጠራር ‹‹ኤሮቢክስ›› (aerobics) የሚባለዉ) ለዕይታ ነርቭ ህዋስ የሚያስፈልገዉን ኦክስጅን ከመጨመር ባለፈ የዓይን ግፊትን(intraocular pressure) ለመቀነስ ይረዳል፡፡ በተለይ ደግሞ የዓይን ግፊት ህመም (Glaucoma) እና ከመደበኛዉ በላይ የሆነ የዓይን ግፊት መጠን (high intraocular pressure) ላለባቸዉ ሰዎች ጥቅሙ የጎላ ነዉ፡፡

ሌሎች የጤና ችግሮችን (ለምሳሌ የስኳር ህመምን) ለመቆጣጠር ስለሚረዳም እንደ ስኳር ያሉ ህመሞች የሚያደርሱትን ቀጥተኛ የዓይን ጉዳት ለመቀነስ ያግዛል፡፡ ስለሆነም በተቻለ መጠን ባለሙያን በማማከር የ30 ደቂቃ እንቅስቃሴ (ለምሳሌ ፈጠን ያለ ጉዞ (jogging)፣ ወዘተ) በሳምንት ለ5 ቀን ማድረግ ተገቢ ነዉ፡፡

ረ. መደበኛ የዓይን ምርመራ ማድረግ

መደበኛ የዓይን ምርመራ ማድረግ የዓይን ጤናን ከመጠበቅ ባሻገር ዓይን መስኮተ ጤና በመሆኑ ስለ አጠቃላይ የጤና ሁኔታ በመጠቆም ወቅታዊና ተገቢ ሕክምና ለማድረግ ድርሻዉ የጎላ ነዉ፡፡ ይህንም ማድረጉ ችግሮችን በቶሎ ለማወቅና ለመታከም ይረዳል፡፡ ምልክት የማያሳዩ የዓይን ህመሞችን (ለምሳሌ፡- ዘገምተኛ የዓይን ግፊት ህመም) ከፍተኛ ጉዳት ሳያደርሱ ለማወቅ ስለሚረዳም ሁሉም ሰዉ ከህጻን እስከ አዋቂ መደበኛ የዓይን ምርመራ ሊያደርግ ይገባል፡፡

# ጤንነት

## የዐይን ጤናን ለመጠበቅ የሚረዱ ዓበይት ተግባራት

ምንጭ መጽሐፍ:- የዓይን ጤናና ክብካቤ በፐ/ር የሺጌታ ገላው ብርሃኑ:- ምዕራፍ 18 ገጽ 191-202 በደራሲዉ ፈቃድ በከፊል የተወሰደ)

እይታ ዉድ፣ ብርቅና ድንቅ የሆነ ለሰዉ ልጅ ጸዳል የሚያላብስ የተፈጥሮ ስጦታ ነዉ:: እንደማንኛውም የሰውነታችን አካል ልንጠብቀዉ እና ልንከባከበው የግድ ይላል::

ከሌሎች የስሜት ህዋሳት ጋር ሲነጻጸር 85 ከመቶ የሚሆነዉን መረጃ ለአንጎል በማድረስ ቀን በቀን ከአካባቢያችን ጋር ለምናደርገዉ የመኖር ትንቅንቅ ወይም መስተጋብር እጅግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርግ የረቀቀና የተወሳሰበ፣ ከፍተኛ እንክብካቤ የሚሻ የብርሃን ስሜት ህዋስ ነዉ:: የዓይን ጤና ችግሮች ሲከሰቱ ወቅታዊና ተገቢ ሕክምና ከማድረግ ባሻገር ችግሮች እንዳይከሰቱ ጥንቃቄ ማድረግና የዓይንን አጠቃላይ ጤና መጠበቅ የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናዎን እጅግ አስፈላጊ ነዉ::

ስለሆነም የዓይን ጤናን ለመጠበቅ የሚረዱ የክብካቤና የጥንቃቄ ድርጊቶችን እንደሚከተለዉ እገልፃለሁ::


### ሀ. ጤናማ የአመጋገብ ሥርዓት መከተል

የተመጣጠነ ምግብ ከሚሰጠዉ ቀጥተኛ ጥቅም በተጨማሪም ከተዛባ የአመጋገብ ሥርዓት ጋር ተያይዘዉ የሚመጡ የጤና ችግሮችን (ለምሳሌ አላስፈላጊ ዉፍረት፣ የስኳር ህመም፣ የደም ግፊት፣ ወዘተ) ለዓይን ጤና አወንታዊ ሚና ይጫወታል:: በተለይም በቪታሚንና በማዕድናት የበለጸጉ ምግቦችን መመገብ የዓይን ልባስ (conjunctiva)፣ የሌንስ (crystalline lens) እና የረቲናን (retina) ጤናና ሥራ የተሳለጠ ለማድረግ ከፍተኛ ሚና አላቸዉ::

ቪታሚንና ማዕድናት በተለይም ቫይታሚን ‹‹ኢ›› (Vitamin E)፣ ቫይታሚን ‹‹ሲ››(Vitamin C) እና ‘ዚንክ’ (Zinc) በዓይን ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ በደም ዉስጥ የሚገኙ ኬሚካሎችን ኃይል ለማዳከምና ከእድሜ መግፋት (እርጅና) ጋር ተያይዘዉ የሚመጡ የዓይን ጤና ችግሮችን (በተለይም የሰገነተ እይታ መጃጀት (Macular Degeneration) እና የዓይን ሞራ (Cataract)) በቶሎ እንዳይከሰቱ ለማድረግና የጉዳቱንም መጠን ለመቀነስ ይረዳሉ::
በቫይታሚን ‹‹ኤ›› (Vitamin A) የበለጸጉ ምግቦች (ጉበት፣ ካሮት፣ ስኳር ድንች፣ ጎመን፣ ቃሪያ፣ ሰላጣ፣ እንጆሪ፣ ማንጎ፣ ወዘተ) ጥራት ያለዉ እይታ እንዲኖር ከማድረግ ባሻገር የዓይን ልባስ ጤናን በመጠበቅና በቂ የዓይን እርጥበት( Eye Moisture) እንዲኖር በማድረግ የዓይን ድርቀትን (Dry Eye) ይከላከላሉ::

ከዚህ በተጨማሪም የዓይን የደም ሥሮችን ቁጣ (inflammation of eye blood vessels) የሚቀንሱና የሰገነተ እይታን ጤናን የሚጠብቁ ምግቦችን (ለምሳሌ ዓሣ፣ የዓሣ ዘይት፣ ወዘተ) መመገብ ጠቀሜታዉ የጎላ ነዉ:: በሳምንት አንድ ጊዜ ዓሣ መመገብ የሰገነተ እይታ መጃጀት ተጋላጭነትን (risk of macular degeneration) በከፍተኛ ደረጃ ሊቀንሰዉ እንደሚችል ጥናቶች ይጠቁማሉ::

ከፍተኛ የቫይታሚን ‹‹ኢ›› መጠን ካላቸዉ በሀገራችን ከሚዘወተሩና አስፈላጊ ከሆኑ ምግቦች ደግሞ ቆስጣ፣ የሱፍ ቆሎ፣ አቮካዶ፣ ዓሣ፣ የወይራ ዘይት፣ ስኳር ድንች፣ ጥቁር እንጆሪና ማንጎ ይገኙበታል:: በተመሳሳይም ለሰዉነታችን የቀን ፍጆታ የሚያስፈልገዉን የዚንክ ማዕድን ከእንስሳትና ከተክል ተዋፅኦ (ለምሳሌ እንጉዳይ፣የዱባ ፍሬ፣ የበግ ሥጋ፣ የዶሮ ሥጋ፣ የስንዴ ቆሎ፣ ቆስጣ፣ ለዉዝ፣ አተር፣ ወዘተ) ማግኘት ይቻላል::




### ለ. ለጤና ጠንቅ ከሆኑ ልምዶች ራስን መጠበቅ

ሲጋራ ማጨስ ለአጠቃላይ ጤና ጠንቅ ከመሆኑም በላይ በሲጋራዉ ጭስ ዉሥጥ የሚገኙ መርዛማ ኬሚካሎች በዓይን ሌንስ፣ ሰገነተ ዕይታ (Macula)፣ ዕይታይ ነርቭ (Optic Nerve) እና የዓይን ደም ስሮች ላይ ጉዳት ስለሚያደርሱ ዕይታን ይጎዳሉ:: ለሌላ የዓይን ጤና ችግርም (የዓይን ሞራ፣ የሰገነተ እይታ መጃጀት፣ ወዘተ) ያጋልጣል:: ስለሆነም ሲጋራ ከማጨስ መቆጠብና የሚያጨሱ ከሆነም ለማቆም መሞከር ተገቢ ነዉ:: ሲጋራ ማጨስ በሚያቆሙበት ጊዜም ለዓይን ጤና ችግር ያለዉ ተጋላጭነት እየቀነሰ ይሄዳል::

የእድሜ መግፋትም ሲጋራ በእይታ ላይ የሚያደርሰዉን ጉዳት እንዲጨምር ያደርጋል:: በአጠቃላይ ሲታይ እድሜ እየገፉ ሲሄድ የሚያጨሱ ሰዎች ከማያጨሱት ሰዎች በሁለት እጥፍ በበለጠ ዕይታቸዉን የማጣት እድል አላቸዉ:: በተመሳሳይ መንገድ የአልኮል መጠጥ አብዝቶ መዉሰድ ሌንስን፣ ሰገነተ እይታንና እይታይ ነርቭን ሊጎዳ የሚችል የኬሜካል ዉህድ ስለሚፈጥር የአልኮል መጠጥ መቀነስ ከተቻለም ማቆም ለዓይን ጤና ድርሻዉ የጎላ ነዉ::

### ሐ. ዓይንን ከአደጋ መጠበቅ

ዓይንን ለአደጋ በሚያጋልጡ ማንኛዉም ዓይነት የሥራ ዘርፎችና ቦታዎች (ፋብሪካዎች፣ የእርሻ ልማት፣ የመኪና ጋራዥ ቤቶች፣ የግንባታ ቦታዎች፣ የብየዳ ሥራ፣ የድንጋይ ፈለጣ፣ የአትክልተኛነት ሥራ፣ ወዘተ)፣ መዝናኛዎችና ስፖርቶች ተገቢ የሆነ የአደጋ መከላከያ መነጽር ማድረግ ያስፈልጋል:: ከዚህ በተጨማሪም ለብርሃን ጨረር መጋለጥ (በተለይም ለልዕለ ሃምራዊ (አልትራቫዮሌት) ጨረር (ultraviolet light/rays)) በዓይን የተለያዩ ክፍሎች ላይ ጉዳት ስለሚያደርስና ለሌሎች ችግሮች (ሞራና የሰገነተ እይታ መጃጀት) ስለሚያጋልጥ ከልእለ ሃምራዊ ጨረር መከላከል የሚችል የፀሐይ መነጽር (UV Protection Sun Glasses) መጠቀም ተገቢ ነዉ::

ሁሉም የፀሐይ መነጽሮች እኩል የመከላከል ብቃት ስለሌላቸዉ የፀሐይ መነጽር ሲገዙ ከ99-100% የመከላከል አቅም ያላቸዉ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ለዕይታም ለፀሐይም የሚሆን መነጽር የሚጠቀሙ ከሆነ ደግሞ ከሌሎች በተሻለ ሁኔታ ቀለማትን መለየት ስለሚያስችል ግራጫ መልክ ያለዉን (በእንግሊዝኛዉ አጠራር ‹‹ፎቶ ግሬይ›› (photo gray glasses) የሚባለዉን) የፀሐይ መነጽር መጠቀም ጥሩ ነዉ:: ከዚህ በተጨማሪም ፀሐያማ በሆኑ አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎች



የአይን ጉዳትን ከመቀነስ እና ከመከላከል አኳያ በኮፒዩተር አጠቃቀም ጊዜ የሚደረጉ ጥንቃቄዎች:

- የኮምፒዩተር አቀማመጥን ማስተካከል፤
- የኮምፒዩተሩን ማሳያ /ሞኒተር/ የቀለም ስብጥርና ደማቅነት ማስተካከል፤
- ነጸብራቅ የሚከላከሉ የሞኒተር ልባሶችን መጠቀም፤
- ሞኒተሩን ከአይራና ከጣት አሻራ የጸዳ ማድረግ፤ የፊደላትን መጠን ከፍ ማድረግና ሞኒተሩን ብዙ ነገር በመክፈት አለማጨናነቅ፤
- በክፍል ዉስጥ በቂ ብርሃን እንዲኖር ማድረግ መቀመጫ ወንበርን ማስተካከል፤
- በተደጋጋሚ የዓይን ቆብን በማርገብገብ የዓይን እርጥበትን መጠበቅ፤
- ለዓይን በቂ ዕረፍት መስጠት፤ የዓይን እንቅስቃሴ ማድረግ፤

መደበኛ የኮምፒዩተር ተጠቃሚ ከሆኑ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የዓይን ምርመራ ማድረግ።

የፀሐይ ባርኔጣ ቢጠቀሙ በፊት ቆዳ ላይ የሚደርሰዉን ጉዳት ከመከላከል ባለፈ በዓይን ላይ የሚያደርሰዉን የጨረር ጉዳት ይቀንሳል::

### መ. የቴክኖሎጅ ምርቶችን አጠቃቀም ማስተካከል

የቴክኖሎጅ ምርቶችን (ኮምፒዩተር፣ ታብሌት፣ ተንቀሳቃሽ ስልክ/ሞባይል፣ መጫወቻ መሣሪያዎች፣ ወዘተ) የሚጠቀም ሰዉ ቁጥር ከመጨመሩም ባሻገር ሰዎች ከእነዚህ ዘመነኛ እቃዎች ጋር ከፍተኛ ቁርኝት በመፍጠር በቀን ብዙ ሰዓታትን እንደሚያሳልፉ መረጃዎች ይጠቁማሉ::

ከአቀማመጥ ጋር በተያየዘም የተለያዩ የጡንቻና የመገጣጠሚያ ችግር (የአንገት ህመም፣ የጀርባ ህመም፣ የትክሻ ህመም፣ የእጅ እጣት ህመም፣ ወዘተ) የኮምፒዩተር ተጠቃሚዎች የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ችግር እየሆነ ነዉ:: በሰለጠነዉ ዓለም የኮምፒዩተር ሱስ ራሱን የቻለ ሕክምና የሚያስፈልግዉ የጤናና የማኅበራዊ ችግር ከሆነም ዉሎ አድሯል:: ለሰዉ ልጅና የቴክኖሎጂ ምርት ቁርኝት ዋነኛ መሳሪያ የሆነዉ ዓይንም የጤና መታወክ ይገጥመዋል::
ረዘም ላለ ጊዜ ኮምፒዩተር ላይ በሚያሳልፉበት ወቅት የቅንድብ መርገብገብ (Spontaneous Eye Blinking) ከመደበኛዉ ስለሚቀንስና በቂ የእንባ ስርጭት ስለማይኖር የዓይን ድርቀት ስሜት ይሰማል:: ከዚህ በተጨማሪም ዓይናችን ለብዙ ጊዜ ተከፍቶ ሲቆይ የእንባ መጠን በትነት (evaporation) ምክንያት ስለሚቀንስ የድርቀት ስሜቱን

ወደ ገፅ 9 ዟሯል

# ኪነ-ጥበብ እና ባህል




በዚያችም ወራት ለእርጉዞች እና ለሚያጠቡ ወዮላቸው፤ ነገር ግን ሽሽታችሁ በክረምት ወይም በሰንበት እንዳይሆን ጸልዩ። የሚለው የቅዱስ መጽሐፍ ቃል ይፈጸም ዘንድ በጋይንት፣ በላሊበላ፣በጋሸና ፣ በቆቦ… ማህበረሰብ የደረሰው የግፍ እና የመከራ ፅዋ ለእኛም እንዳይቀርብን ይመስላል እሁድ ነሃሴ 2 ቀን 2013 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 8 ሰዓት አካባቢ ወደ 13 የሚሆኑ የአሸባሪውና ዘራፊው የሕውሀት ቡድን ከእኛ ከተማ (መርሳ) ገቡ።

እኒህ ወራሪዎች ሲቪል ለብሰው በመምጣታቸው የከተማዋ ነዋሪም በቀላሉ ሊለያቸው ስላልቻለ አገር አማን ብሎ የተለመደ የዕለት ከዕለት ተግባሩን እያከናወነ ነበር።በአካባቢው የሚኖረው አርሶ አደሮች ግን ጥርጣሬያቸውን ለአንዳንድ የከተማ ነዎሪዎች ለመጠቆም ቢሞክሩም ከተሜው የሸሹ የእኛ ሰራዊቶች ሊሆኑ ይችላሉ በማለት ተዘናጋ። ከምሽቱ 3:00 አካባቢ በድንገት የተኩስ ሩምታ ይወርድ ጀመር። ሰላማዊው የከተማዋ ነዋሪ በከፍተኛ ድንጋጤ እና ሽብር አገሪቱን ለቆ ለመውጣት እግሩ ወደ መራው ለመጓዝ መተረማመስ ጀመረ እኔም ከእነርሱ መካከል አንዷ ነበርኩ።

የከተማዋ ወጣቶች ከመሸሸ ይልቅ ጠላትን መታገል እንዳለብን በማመን መኪና እንዳይወጣ መንገዱን በድንጋይና በግንድ አጠሩት።

ወዲያው የመከላከያ ልብስ የለበሱ ሰዎች መጡ።እኔ እና ጎረቤቶቼ በጭንቀት ተውጠን ወደ ቤታችን በመመለስ የከፋ ነገር ከመጣ ይዘነው የምንወጣ ጥቂት ልብስ እና አንዳንድ በጣም ያስፈልጉናል ያልናቸውን ነገሮች ለማዘጋጀት አንዱን ማንሳት አንዱን መጣል ጀመርን ፣ውስጣችን በፍርሃት ስለተሞላ ግራ ተጋብተናል፤በመጨረሻም ብንሞትም አብረን እንሙት ብለን ከአንድ ቤት ውስጥ ሰባት ሆነን በፍርሃት እየተንቀጠቀጥን ነፍሳችንን ለአምላካችን አደራ ሰጥተን ቁጭ አልን።

በወገን ጦርና በጠላት ጦር መካከል ተኩሱ እንደ ቀጠለ ነው ። ከምሽቱ 10 ሰዓት አካባቢ የጠላት ሀይል ከተማዋን ተቆጣጠረ። እንዳይነጋ የለም በጭንቀት እንደተዋጥን ነጋ። ነሃሴ 3 ሰኞ ጧት ተነስተን የተወሰኑ አልባሳትን ብቻ በሻንጣ በመያዝ ያደግንበትን፣ የቦረቅንበትን፤ ደስታ እና ሀዘን ያሳለፍንበትን ቀየ በቅጡ እንኳ ዞር ብለን ለማየት ሳንሞክር፣በስንት ውጣ ውረድ ያጠራቀምነውን ጥሪት እንደዋዛ ጣል አድርገን፤ ህይወትን ለማትረፍ ወደ ደሴ ለመሰደድ በጭንቀት ከቤታችን ወጣን።

ትራንስፖርት ለማግኘት ብዙ ጣርን ነገር ግን መኪና ያለውም የራሱን ቤተሰብ እና ዘመድ እየያዘ መሄድ እንጅ እኛን መውሰድ የሚፈልግ አካል አላገኘንም። እየዘገየን በሄድን ቁጥር አዳጋ እንዳይደርስብን በመፍራት በእግራችን ጉዞ ጀመርን።




ከመካከላችን ነፍሰ ጡሮች ፣ህጻን ያዘሉ እናቶች እና አቅመ ደካሞች ይገኙበታል።

ቀንም፣ ሌትም፣ እግሬ አውጭኝ ወደፊት ብቻ፤የደከመው ወደኋላ ሲቀር ጠንከር ያለው ሲቀድም ፊት እና ኋላ እየሆንን ጉዟችን ቀጠልን…ነፍስን ለማትረፍ ህይወት ለማስቀጠል። "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" እንዲሉ የክረምት ወቅት መሆኑ ከድካማችን በተጨማሪ ከላይ ዝናቡ ከታች ጎርፉ ሌላ ችግር ፈጥሮብን ነበር።በሻንጣ የተሸከምነው ልብስ በዝናቡ ሲበሰብስ ክብደቱ ስለሚጨምር ከሻንጣ አውጥተን እንጨምቅና እንደገና እንሸከመዋለን።

ይህን ድርጊት ዝናብ በዘነበ ቁጥር እናከናውናለን።የጠላት ሰራዊት እንዳያገኘን በመፍራት አስፓልቱን ትተን መንገዳችን ጫካ ለጫካ በመሆኑ ሌሊት በምንጓዝበት ጊዜ አቅጣጫ እንስታለን ፤ሲነጋ ከፊታችን አንዲት ሁለት አመት አካባቢ የሚሆነው ህጻን ያዘለች እናት ትጓዝ ነበር፣አይዞሽ ብለናት ፈጠን ፈጠን እያልን ከኋላ ትተናት መጓዝ ጀመርን፣ተኩሱ አሁንም ተደገመ ፤ዘወር አልን ያቺ ምስኪን እናት ልጇን እንዳዘለች በደረቷ ድፍት ብላለች፤ህጻኑ ከጀርባዋ ሆኖ እርሪ… እርሪ…በማለት ያለቅሳል፤እኔ ወደ ህጻኑ ልመለስ ስል ጓደኞቼ እጄን ጎተቱኝና የተሸከምነውን ልብስ ጥለን ከሚተኮሰው ጥይት ለማምለጥ ዝግዛግ እየመታን የሰቆቃ ጉዟችን በሩጫ ቀጠልን።

እኒህ ከሰው የተፈጠሩ የማይመስሉ ልክፍተኞች በመንገድ የሚያገኙትን ሁሉ ያለ ርህራሔ ይገድሉ ነበር።

እኔ ወደ ፊት ብሸሽም ሀሳቤ ግን ወደኋላ ይጎትተኛል፤ ወደ ህጻኑ ልጅ ፤አሁንም ለቅሶው ከህሌናየ ሊጠፋልኝ አልቻለም እርሪ… እርሪ…ከበድን የእናቱ ጀርባ ሆኖ የሚያሰማው የሰቆቃ ፣የድረሱልኝ ልቅሶ።ምን ሆኖ ይሆን? ሌላ የጠላት ሰራዊት መጥቶ ይገድለው ይሆን? አውሬ ይበላው ይሆን? እራብ ይገድለው ይሆን? ወይስ እንደ እኛ ያለ ስደተኛ ጠላት ካለፈ በኋላ ጊዜ ጠብቆ ያነሳው ይሆን?… አላውቅም ብቻ ብዙ ጥያቄዎች በአዕምሮዬ ውስጥ እየተመላለሱ እረፍት ነሱኝ።

ፈጣሪ ሆይ ትዕግስትህ ምን ድረስ ነው? የንጹሀን ደም በከንቱ ሲፈስ፣ የዕምነት ቦታዎች ሲረክሱና ሲወድሙ፣…አሁን ደግሞ ይህ ህጻን? ውስጤ በሀዘን ስብርብር አለ።

ምን እንደማስብ አላውቅም በፈጣሪ ስራ መግባት ስተት እንደሆነ አውቃለሁ፤ ነገር ግን ህጻኑ ጫካ ውስጥ ብቻውን የቀረው ሰላሜን ነስቶኛል…ወደ ፊት አድጎ ለአገር አለኝታ ለወገን መከታ ይሆናል በማለት እናት በጀርባዋ አዝላ ብርድና ድካሙን ተቋቁማ ከፈጣሪ የተሰጣትን አደራ ለመወጣትና የእርሷንም ነፍስ ለማትረፍ ስትደክም የነበረ እናቱን አጥቷል፤ ብቻ ፈጣሪ ይድረስለት እንጂ ምን እላለሁ? እኔማ ደካማ ፍጡር በመሆኔ የእኔን ህይዎት ለማትረፍ ስል ጨክኘበታለሁ ፤ህሌናዬ ግን ሁልጊዜ ሲወቅሰኝ ይኖራል።

ስድስት ቀን በእግራችን ከተጓዝን በኋላ በሰባተኛው ቀን ማርሶ ቢሌ ከምትባል ቦታ እስከ ሀይቅ የሚያደርሰን መኪና አገኘን፣የ5 ብሩን ትራንስፖርት 50 ብር ከፍለን ሀይቅ ደረስን፤ከዚያም ከሀይቅ እስከ ደሴ የ15 ብሩን ትራንስፖርት 100 ብር በመክፈል ደሴ በሰላም ገባን።

በዚህ ሰአት መኪና ማግኘታችንን እንጂ ዋጋ ለመከራከር አላቅማማንም ምክንያቱም የእኛ አላማ ቦታውን በፍጥነት ለቀን ህይወታችንን ከጨካኙና ከአሸባሪው የህውሀት ቡድን ቅጣት ለማዳን ሲሆን ወገናችን ብለን በስደት ከምንጠጋበት አካባቢ ደግሞ አንዳንድ ሆድአደር እና ስግብግብ አጋጣሚውን በመጠቀም ለመበልጸግ ሲሞክሩ አይተናል።

ደሴ እንደ ደረስን ህይወታችንን ከሙታን መካከል በተዓምሩ ፈልቅቆ ስላተረፈልን ፈጣሪያችንን በእጅጉ አመሰገንን። ታምሜ "መሰረት" የሚባል የግል ጤና ጣቢያ እንደገባሁ በድንገት ስልኬ ሲጠራ አነሳሁት፡

ወደ ገፅ 12 ዞሯል

## ህዝቡ በባዶ እጁ... ከገፅ 7 የቀጠለ

እንዲሆኑ እንዲሁም በእውቀት ላይ እንዲመሰረቱ መስራት አለብን።

ሲስተም ካልጠነከረ በሩጫ የሚሰሩ ሥራዎች በሙሉ ከልምድ የሚገኙትን ለመቀመር የማይመቹና ከነበረው በላቀ ሁኔታ እንዳንሄድ የሚያስችሉ ሥለሆነ ሩጫ እንጅ ጠቀሜታና ውጤት ሊኖራቸው አይችልም። ስለዚህ ምሁራን በዚህ ላይ መስራት ይጠበቅባቸዋል።

ፕሮፌሰር ፈንቴ ተሞክሯቸው በመነሳት ተመሳሳይ ችግር የገጠማቸው ሀገራትን በማንሳት እንደምሳሌ በማንሳት የአገራችን ሁኔታእንዲገልፁልንጠይቀናቸዋል።

የርስበርስ ጦርነት የገጠማቸው ሀገሮች በጣም ብዙ ናቸው። በጥልቀት ሲታይ ግን የኢትዮጵያ ሁኔታ ከዓለም የተለየ ነው።

በመጠኑም ቢሆን የሚመሳሰለው የኮሶቦ ወይም የቀድሞዋ (ዩጎዝላቪያ) ሁኔታ ነው። እ.አ.ዘመን አቆጣጠር 1999 ኮሶቦ ወይም በቀድሞ ስሟ (ዩጎዝላቪያ) 6% ሰርቦች ነበሩ። እኒህ 6% ሶርቦች 94% አልባኒያዎችን ይጨቁናቸው ነበር።

እንዳይማሩ አመራር ቦታ ላይ እንዳይቀመጡ በከፍተኛ ደረጃ ጨቁነውይዘዋቸውነበር።

የሕዝብ ቁጥራቸው አጠቃላይ 2.2 ሚሊዮን ነበር በወቅቱ አውዳሚ ጦርነት ተከሰተና ተቋማት የጤና እና የትምህርት ተቋማትን ጨምሮ በከፍተኛ ደረጃ ወደሙ። ጦርነቱ የተቋጨው (NATO) የሰሜን ጦር ቃልኪዳን ድርጅት ሀይል አስገብቶ ነው የጦርነቱ መቋጫ ያደረገው።

እዚህ ላይ ከኢትዮጵያ ጦርነት የሚለየው የኮሶቦ ጦርነቱ ሲቆም ለ2.2 ሚሊዮን ህዝብ ከ400 በላይ የእርዳታ ድርጅቶች ገብተው ነበር

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአስተዳደሩን ተልዕኮ በጊዜያዊነት ይምራው ተብሎ ሥራውን ይዞት ነበር። የተመዘገበው ውጤት ተጨማሪ ውድቀትና የሥነ-ልቦና ስብራት ነበር ያመጣው።

400 ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች ገብተው ሥነ-ልቦናቸውን ድቅቅ አድርገውት ማስተባበር ሳይችል ቀረ። ትምህርትና ጤና እንደወደቁ ቀሩ ዋና ምክንያት ከሀገሪቷ የተገኘው ጠንካራ ሲስተም የመፍጠር አጋጣሚ ሀገሪቱ መጠቀም ባለመቻሏ ነበር።

ይህንን ወደኛ ሀገር ተጨባጭ ሁኔታ ስናመጣው አስቀድመን በድል አድራጊነት ተጠናቆ በኋላ ወደሌላ ኪሳራና የስነ-ልቦና ሥብራት እንዳንሄድ አስቀድመን መንግስት ሲስተም ተከትሎ እንዲሰራ ከክልል እስከ ወረዳ ድረስ ያለውን የጥናት ስራዎችን የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ እየሰራ ነው። በክልል ደረጃ ፎርም ወርዶ ፈጥነን የጤና እና የትምህርት ሲስተም እንዲጠናከሩ አስቀድመን አዘጋጅተነዋል።

ወገኖቻችን፣ አርበኞቻችን ግንባር ላይ ሲዋጉ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ መምህራን በቡድን ከጦርነት በኋላ የሚገጥመውን ነገር በአንድ ላይ ሁነን እየሰራን ነው።

ባወጣነው ፍሬም ወርክ መሰረት የኒቨርሲቲዎችና ሌሎች ምሁራን የጤና ሲስተም፣ የት/ት ሲስተም እንዲጠናከሩና ማንኛውም ግብረ-ሰናይ ድርጅት የሚሰራውን ነገር መቆጣጠርና መምራት እንዲችሉ ማድረግ ያስፈልጋል።

ያለበለዚያ ለኢትዮጵያም ሌላ ችግር ሊፈጥር ይችላል። ከኮሶቮ/ ዮጎዝላቢያ ለቀሪው የዓለም ክፍል የተገኘው ትምህርት ይህ ነው።

የነበረውን የሥነ-ልቦና ክፍተት ለማጣናከር የሚቻለው ከሌሎች ሀገሮች የሚገኘው ልምድ በመውሰድ ጠንከር ያለ ሲስተም ፈጥሮ በአጋባቡ መመራት እንዳለበት መረዳት አለብን።

ጦርነቱን ተከትሎ ለሚመጣው ችግር በርካታ ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት በስርዓት የሚመራ ኢንተርቬንሽን የሚያስፈልገው ችግር ነው። አሁን ያሉ ችግሮችና የተለያዩ መስሪያ ቤቶች ቀበሌ ድረስ አደረጃጀቶቻቸውን ማጠናከር አለባቸው። እኛም እየሰራን ያለነው ይህንኑ ነው።

የከፍተኛ ት/ት ተቋማት ይህንን ማገዝና በመረጃ ላይ የተመሰረተ የመፍትሔ አሰራር ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ አለባቸው።

መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መንግስት ባወጣው መመሪያ መሠረት ብቻ መንቀሳቀስ አለባቸው።

አዛዥ ፈላጭ ቆራጭ አይነት ወይም እንደፈለጉ የሚገኙበት አይነት አካሄድ መኖር የለበትም።

መንግስት ቀበሌ ላይ የቀበሌ መስተዳድር ነው በእሱ ስር ገብተው መስራት አለባቸው



ፕ/ር ፈንቴ አንባው የዓዕምሮ ጤና ህክምና ኢፒዲሞሎጅስት

እንጂ የፈለጉትን ከልክለው ወይም አዘው የሚያሰሩበት የቤተኛ ጠላት አሰራር መታረም አለበት።

ኢህአዲግ ካደረሰው ጉዳት ዋናው የተበላሸ አሰራር ባህል ማድረጉ ነው። ከእያንዳንዱ ፕሮጀክት መስረቅ የሚፈልጉ ቢሮክራት ብዙ ነው። ይህንን የሚታገል ከምሁራን መካከል ፋኖ ያስፈልጋል። በመረጃ ላይ የተደገፈ ትግል ያስፈልጋል።

ህዝቡ በባዶ እጁ ከስናይፔር ጋር ተናንቆ ያመጣውን ድል በሌሎች ድክመት ለፍሬ ካልበቃ የስነ-ልቦና ሥብራቱ ለክፍለ ዘመን ሊያስነክስ ይችላል። ለጥገናም የሚያስቸግር ይሆናል። የተግባቦት እና መገናኛ ብዙሀን ሰዎች ንብረት የወደመበትን፣ ቤተሰብ የተሰዋበትን እና ያዘነውን ወገን የስነ-ልቦና ሥብራት እያሉ መጥራት ማቆም ያስፈልጋል። የቃላትን አጠቃቀማችን ማስተካከል አለብን። ጀግና ተመልሶ ድል እንዲያስመዘግብ ከተፈለገ ተሸንፈናል የሚያስብል የቃላት አጠቃቀምን ማረምና ማስተካከል ያስፈልጋል።

## የጉዞ ማስታወሻ

ከገፅ 11 የቀጠለ

በፊት ፋብሪካ አብረውኝ ይሰሩ የነበሩ የኮምቦልቻ ነዋሪ ነበሩ።

ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ መርሳ በጠላት መያዟን ስለሰሙ ደህንነቴን ለመጠየቅ እንደደወሉ ነገሩኝ ። እኔም ደሴ መግባቴን እና ያለሁበትን ሁኔታ ነገርኳቸው ። እርሳቸውም ከባለቤታቸው ጋር በመሆን ካለሁበት ቦታ ድረስ መጥተው ሳምንት ጤና ጣቢያ ካስታመሙኝ በኋላ ወደ ቤታቸው በመውሰድ ሀገራቸው በጠላት ሀይል እስከምትያዝ ድረስ ከቤታቸው በእንክብካቤ አቆዩኝ።

ለእነርሱ እኔን መንከባከባቸው ከምንም ባይቆጥሩትም ለእኔ ግን ከባድ ሸክም ነበር፤መፍትሔ የሌለው ጭንቀት....እኔን ስደተኛዋን ምንም እንዳይሰማኝ ለማድረግ አይዞሽ አለንልሽ እያሉ ሲያበረታቱኝ እንዳልነበረ ለእነርሱም የእኔ እጣ ፈንታ ደረሳቸው። በጣም አዘንኩ። ከዚህ የተሻለ ሀሳቤን የሚገልጽልኝ ቃል ባገኝ ደስ ይለኝ ነበር። በሀዘን ላይ ሀዘን እንደ ድንጋይ ካብ ተደራረበብኝ፡ደሴ መያዟን ስንሰማ ኮምቦልቻን ሳይደርሱ መሸሽ እንዳለብን ወሰንን።

ተቃቅፈን ተላቀስን፣ ተላቅሰን... የግድ መላቀቅ ነበረብን ተላቀቅንና ወዴት መሸሽ እንዳለብን ተነጋገርን፤ እነርሱ አዲስ አበባ ልጅ ስላላቸው ወደ አዲስ አበባ፤እኔ ደግሞ ወደ ባህርዳር ለመሄድ ወሰንን። እኔም ስለነበረኝ ቆይታ፣ ስላደረጉልኝ ነገር ሁሉ ከልቤ እያለቀስኩ አመሰገንኳቸው።

እነርሱ ግን በዚያች ሰዓትም ለእኔ ያስቡ ነበር። ለሰጭ ሁሉ ነገር ቀላል ነው ለተቀባይ ግን ይከብዳል በምንሄድበት ቸር እንዲገጥመን እና ፈጣሪ ሰላም አስፍኖ ዳግም እንድንገናኝ ተመኝተን ተለያየን።

እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ ስደት ተጀመረ። ገና መንገድ ሳስብ ውስጤ ድክምክም አለ፤ይሄስደት መቼ ይሆን የሚያበቃው...? አልኩ በሀሳቤ። ከኮምቦልቻ፣በመካነ ሰላም፣ መርጦለማርያም፣ ሞጣ አድርጌ ወደ ባህርዳር መጣሁ። ከዚያም ከሌሎች ስደተኞች ጋር በመሆን ዘንዘልማ ካለው የስደተኞች ማቆያ የተለያዩ መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ለምግብነት የሚሆኑ ነገሮች፣ለንፅህና መጠበቂያ የሚያገለግሉ፣ ለመተኛ የሚያገለግሉ ቁሳቁስ እርዳታ እየተደረገልኝ ፣ስታመምም ከዚያው የህክምና እርዳታ እየተሰጠኝ በተስፋ ቆየሁ።

ዛሬ በጣም ተደስቻለሁ ፈጣሪ ክብሩ ይስፋ! ከተማችን ነጻ ወጥታለች። ሰሞኑን ሳንመለስ አንቀርም ፤ግን ደግሞ ውስጤን ፍራት፡ ፍራት ይለኛል። ገንዘብ ተሰርቶ ይገኛል የሰው ልጅ ግን...?እነማንን በህይወት አገኛቸው ይሆን? እነማንንስ...?

---ስሟ እንዲጠቀስ ያልፈለገች

# የሳይንስ ጥግ

ይህ አምድ ሳይንስ እና ቴክኖሎጅ ነክ የሆኑ ፅሁፎች ይቀርብበታል

# What is a Drone?

A drone is an unmanned aircraft. Drones are more formally known as unmanned aerial vehicles (UAVs) or unmanned aircraft systems. Essentially, a drone is a flying robot that can be remotely controlled or fly autonomously using software-controlled flight plans in its embedded systems, that work in conjunction with onboard sensors and a global positioning system (GPS).

UAVs were most often associated with the military. They were initially used for anti-aircraft target practice, intelligence gathering, and more controversially, as weapons platforms. Drones are now also used in a range of civilian roles, including the following: search and rescue, surveillance, traffic monitoring, weather monitoring, firefighting, personal use, drone-based photography, videography, agriculture, delivery services

### How do drones work?

Drones have two basic functions: flight mode and navigation. To fly, drones must have a power source, such as a battery or fuel. They also have rotors, propellers, and a frame. The frame of a drone is typically made of a lightweight, composite material to reduce weight and increase maneuverability. Drones require a controller, which lets the operator use remote controls to launch, navigate and land the aircraft. Controllers communicate with the drone using radio waves, such as Wi-Fi.

A typical unmanned aircraft is






made of light composite materials to reduce weight and increase maneuverability. This composite material strength allows military drones to cruise at extremely high altitudes. UAV drones are equipped with a different state of the art technology such as infrared cameras, GPS, and laser (consumer, commercial and military UAV). Drones are controlled by remote ground control systems (GSC) and also referred to as a ground cockpit. An unmanned aerial vehicle system has two parts, the drone itself and the control system. The nose of the unmanned aerial vehicle is where all the sensors and navigational systems are present. The rest of the body is full of drone technology systems since there is no space required to accommodate humans. The engineering materials used to build the drone are highly complex composites designed to absorb vibration, which decreases the sound produced. These materials are very lightweight.

### What Is A Drone And UAV Technology

Below we examine the science and drone technology behind the DJI Phantom UAV. We also have plenty of information on the latest drone technologies from the newest drones on the market. There are plenty of links, where you can read deeper into various components of drone technology. For example, here is a terrific drone components overview article. This gives information on the individual components seen in most drones.

### Drone Types And Sizes

UAV drones come in a wide variety of sizes, with the largest being mostly used for military purposes such as the Predator drone. The next in size is unmanned aircraft, which have fixed wings and require short runways. These are generally used to cover large sections of land, working in areas such as geographical surveying or to combat wildlife poaching.

# ስብጥር

ይህ አምድ በሌሎች አምዶች ያልተስተናገዱ ልዩ ልዩ ፅሁፎች ይቀርብበታል



*Dr. Hirut Assaye; Director, Technology Transfer and Universiy-Linkge*

We are here to introduce you the concepts of Technology Transfer and University-Industry Linkage for easy communication and collaboration with our office.

## Technology Transfer

Let's start by defining what Technology is first! We just pick only few from a dozen of its definitions.

'Technology is the systematic application of scientific knowledge for practical purposes.'

'Technology is a set of knowledge contained in technical ideas, information and data, personal technical skills and expertise, equipment, prototypes, designs or computer codes.'

'Technology can be knowledge, knowhow, procedure and system related to manufacturing and use of goods and services that are necessary to solve the economic and social problems of a given society and to improve its living standard.'

The above definitions show that technology consists of two main components:

1) A physical component which comprises of items such as products, equipments, blueprints, techniques, and processes; and 2) Informational component which consists of know-how in management, marketing, production, quality control, reliability, skilled labor and functional areas.

In fact, technology is dynamic by its nature and its definition varies according to context of disciplines. For-instance:
In Health, technology is defined as the application of organized knowledge and skills in the form of devices, medicines, vaccines, procedures and systems which are developed to solve a health problem and improve quality of lives. In Business, technology can be something related with customer-facing applications and solutions, business-critical production and logistics solutions, or back office financial systems, etc.

In Agriculture, technology refers to application of techniques to control the growth and harvesting of animal and plant products.

In Social sciences, technology is defined as applying the use of social science theories and methods and implementing related technologies for specific purposes especially social ones in order to ease social procedures.

In Engineering, technology is the application of scientific and engineering knowledge and methods combined with technical skills in support of engineering activities.

## What is Technology Transfer then?

Technology transfer is the process of sharing skills, knowledge, technologies, methods of manufacturing, intellectual property rights, samples of manufacturing and facilities to the public or other institutions to ensure that scientific and technological developments are accessible to a wider range of

**Continued to page 6**






# እንግዳ

ይህ አምድ የዩኒቨርስቲው ሰራተኞች፣ ተማሪዎች ወይም ሌሎች ታዋቂ እና ተፅኖ ፈጣሪ ሰዎች በዕንግድነት ይቀርቡበታል

## ‘‘ያለምሁራን ተሳትፎ የትኛውም አለም አንድ እርምጃ ወደፊት አይራመድም’’

በአለባቸው አለሙ

በዚህ አምዳችን የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራንን ክብር፤ መብትና ተጠቃሚነት በምን ሁኔታ ላይ ይገኛል በሚለው ርእሰ ጉዳይ ላይ ከእንግዳ ጋር ቆይታ የምናደርግ ይሆናል፡፡



አቶ ፈለቀ ወርቁ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ መምህርና የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ማህበር ፕሬዚዳንት

**ናይል፡-** በቅድሚያ ለቃለ-ምልልሱ ፈቃደኛ በመሆንዎ በናይል ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ስም እያመሰገንን ሙሉ ስምዎትንና የስራ ኃላፊነዎትን ቢያስተዋውቁን?
አቶ ፈለቀ፡- ስሜ አቶ ፈለቀ ወርቁ ሲሆንኃላፊነቴደግሞ በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የኦርጋኒክ ኬሚስትሪ መምህርና የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ማህበር ፕሬዚዳንት እንዲሁም የአማራ ክልል ዩኒቨርሲቲዎች መምህራን ማህበር ሰብሳቢ ነኝ፡፡

**ናይል፡-** የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራንን ክብር፤ መብትና ተጠቃሚነትን በተመለከተ ጥናት እየተደረገ እንደሆነ ሰምተናልና እርስዎም የጥናት ቡድኑ አባል እንደመሆንዎ ቡድኑ እየሰራ ያለው ምንድን ነው?
አቶ ፈለቀ፡- አሁን እየተሰራ ያለው የመምህራንን ሁለንተናዊ ጥቅም ለማስጠበቅ የሚያስችል ጥናት ማለትም ከፍተኛው የትምህርት ጣራ የደረሱ ፕሮፌሰሮች፤ ረዳት ፕሮፌሰሮች፤ ተባባሪ ፕሮፌሰሮች፤ ሌክቸረሮችና ሌሎችንም ምሁራን አከፋፈል አካቶ ተገቢው ክፍያ እየተከፈለ ለማድረግ ያለመ ነው፡፡ ከምስራቅ አፍሪካ ሀገሮች የተወሰኑትን የክፍያ ሁኔታ ብንመለከት ለሙሉ ፕሮፌሰር የሚከፈለውን ለምሳሌ ኬንያ 2,838 ዶላር፤ ሩዋንዳ 5,200 ዶላር፤ ታንዛኒያ 3,600 ዶላር፤ ዩጋንዳ 1,320 ዶላር፤ ደቡብ ሱዳን 2,120 ዶላር፤ ኢትዮጵያ 448 ዶላር እንደሚከፍሉ ከዚህ በፊት የተደረጉ ጥናቶች ያሳይሉ፡፡ ኢትዮጵያ ከምስራቅ አፍሪካ ሀገራት መካከል አንዷ እንደመሆኗ መጠን በእውቀት፤ በአመለካከት፤ በስብዕና ልዕልና የተሞላውን ምሁር ተገቢ ክፍያ ባለመክፈሏ፤ ክብርና ዝና ያለውን የመምህርነት ሙያ በርካታ ምሁራን በመልቀቅ ወደውጭ ሀገር ፈልሰው ይሄዳሉ፡፡

ስለሆነም ልምድ ያላቸው መምህራን ሲለቁ ልምድ የሌላቸው መምህራንን በመተካት ለማሟላት የሚደረገው ጥረት ጥሩ ቢሆንም በትምህርት ጥራት እና ብቁ ዜጋ ማፍራት ላይ የራሱ አስተዋፆ አለው፡፡ ስለሆነም ለመምህራን ልምድና እውቀት ትኩረት ማድረግ በጣም ተገቢ ነው፡

ለመምህራን የሚሰጠው ትኩረት አናሳ መሆን የተሟላ ስብዕና ያለው፤ ሀገር ወዳድና ወንድም አማችነትን የሚያቀነቅን እና ህብረ ብሄራዊነትን የሚገነባ ትውልድ በተገቢው መንገድ እየተቀረጸ አይደለም፡፡ ስለዚህ የመምህራን መሰረታዊ ፍላጎት አለመሟላትና የኑሮ ውድነትን ከማሸነፍ አንጻር ጥያቄ ውስጥ መግባት ምሁራን መደበኛ የመማር ማስተማር ስራቸውን፤ የጥናትና ምርምር ስራዎችንና የማህበረሰብ አገልግሎትን በማስፋፋትና ለህብረተሰቡ በማስረጽ የሀገራችን ችግር በሚጠበቅባቸው ልክ እንዳይፈቱ ተጽእኖ አሳድሯል፡፡

የክፍያ ስርአቱን በተመለከተ የተጠየቁ አንኳር ጥያቄዎችን በመለየት ለ6 የፌደራል መስሪያ ቤቶች ማለትም ለትምህርት ሚኒስቴር፤ለገንዘብ ሚኒስተር፤ ለገቢዎች ሚንስተር፤ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን፤ ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት እና ለኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አቅርበናል፡፡

**ናይል፡-** የመምህራን ችግር እንዲፈታ የመምህራን ማህበር ምን እንቅስቃሴ አደረገ?
አቶ ፈለቀ፡- እንደ መምህራን ማህበር ስራችን በአግባቡ በመስራት የትምህርት ጥራትንና ተደራሽነትን እ ያ ስ ጠ በ ቅ ን ጥ ያ ቄ ዎ ቻ ች ን በወኪሎቻችንአማካኝነት እንዲፈቱ በተደጋጋሚ አቅርበናል አሁንም በማቅረብ ላይእንገኛለን፡፡
ናይል፡- በወቅቱ የቀረቡት ጥያቄዎች ምንምን ናቸው?


አቶ ፈለቀ፡- የቀረቡት መ ሰ ረ ታ ዊ ጥ ያ ቄ ዎ ች በሁለት ይከፈላሉ እነሱም፡-

1ኛ. ክብርንእና ሀለፊነትን በተመለከተ፡-
ይህም ሲባል ምሁራን በሀገር ግንባታ ላይ፤ ሀገር ተሻጋሪ የዲፕሎማሲ ስራ ላይ፤የፖሊሲና ስትራቴጅ ቀረጻና ዝግጅት ላይ፤በአገር ልማት ላይ፤ ሀገር ችግር ውስጥ በገባችበት ጊዜ መፍትሄ ማፈላለግ ላይ ወዘተ ትኩረት ተሰጥቷቸው እንዲሳተፉ አለመደረጉ ተገቢ አይደለም፤ በአጠቃላይ በሁለንተናዊ የአገራችን ፖለቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ከማንም በበለጠ የባለቤትነት ስሜትና ሀላፊነት ተሰምቶት እንዲሰራ አለመደረጉ በመምህራን ላይ ቅሬታ ሲፈጥር ቆይቷል፡፡

2ኛ. የመምህራን መብትና ጥቅማጥቅም በተመለከተ፡- በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ሲታይ ተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ ኖሯቸው በልማት ድርጅቶች፤የሚሰሩና በቦርድ የሚተዳደሩ መስሪያ ቤቶች ለምሳሌ ባንኮች፤ ገቢዎች፤ የመ ሳሰሉት ከአንድ ዩኒቨርሲቲና የሀገር ዋልታ ሆኖ በእውቀት፤ በክህሎትና በአመለካከት ምዕሉ የሆነው ምሁርና ተመራማሪ ከሚያገኘው ክፍያ ከሦስት እጥፍ በላይ ደመወዝ ይከፈላል፡፡

ስለዚህ መንግስት ለከፍተኛ ት ም ህ ር ት ተ ቋ ማ ት ና ዩኒቨርሲቲዎች ከፍተኛ የልማት ድርጅቶች መሆናቸውን ተረድቶ የደምወዝ ማሻሻያ እንዲያደርግ፤ የደምወዝ ክፍያውም በዶላር እንዲሆን ጥያቄ አቅርበናል፡፡ የቤት አበል ክፍያም ታክስ የተደረገና የሚደርሰው የክፍያ መጠን 650 ብር መሆኑ በአሁኑ ወቅት ካለው ጣራ የነካ የኑሮ ውድነት አንጻር ሲታይ ፍትሐዊነት የሌለውና ሌሎች እንደባንክ ያሉ የልማት ድርጅቶች የሚከፍሉት የቤት አበል ከ10 ሺህ ብር በላይ፤ ሀኪሞች ስፔሻላይዝድ ዶክተሮች ከ10ሺህ ብር በላይ፤ ለሚዲያ ባለሙያዎች ደግሞ 8ሺህ ብር ሲሆን ዳኞች በየደረጃው ከ5ሺህ ብር ጀምሮ ይከፈላቸዋል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተቀጥረው ከ1-12ኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን የቤት ኪራይ 3,000 ብር እየተከፈለ እያለ ለዩኒቨርሲቲ መምህራን ግን ትኩረት ባለመሰጠቱና ጥቅሙ ባለመከበሩ ማበርከት የሚጠበቅበትን አስተዋጽኦ በአግባቡ ሳይወጣ እየቀዘመ ይገኛል፡፡ በሀገር ግንባታ ስራ ላይም ትልቅ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡

ወደ ገፅ 8 ዞሯል


ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ
Bahir Dar University
1963
ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ
Wisdom at the source of the Blue Nile
Welcome back, students!